# የእምነት አንቀጾች

*የአስተምህሮና የስነ ምግባር መጽሐፍ* ¶ 106

¶ 106. የግሎባል ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች።

የእምነት አንቀጾች የግሎባል ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን መመሪያ የሆኑትን የአስተምህሮ መስፈርቶች ይደነግጋሉ። በመሆኑም፣ የዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያንን የእምነት መግለጫዎች ወግ ያረጋግጣሉ፣ የፕሮቴስታንት እምነት ሥነ መለኮታዊ ቅርሳችንን ይገልጻሉ፣ የቤተ ክርስቲያናችንንም ልዩ የዌስሊያን-ሜቶዲስት አጽንዖቶችና አንድ አንድ ጉዳዮችን በግልጽ ያስቀምጣሉ። የእምነት አንቀጾች ለትክክለኛው ክርስቲያናዊ እምነት ያለንን ቁርጠኝነት ቢገልጹም፣ የኒቅያ የእምነት መግለጫ (381 እ.ኤ.አ.) በመጀመሪያው ቋንቋ መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደሚወጣ እንደገለጸ፣ እንዲሁም በዓለም ዙሪያና በግሎባል ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ ከወልድም እንደሚወጣ የሚገልጸውን ተጨማሪ መግለጫ እንዳልተቀበሉ እንገነዘባለን። ዓለም አቀፋዊ ባሕሪውን በማንጸባረቅ፣ ግሎባል ሜቶዲስቶች የኒቅያን የእምነት መግለጫ በአምልኮም ሆነ ለእምነት መመሪያነት ሲጠቀሙበት “እና ከወልድም” የሚለውን ሐረግ ለማካተት ወይም የመተው ነጻነት አላቸው (¶105)። የኒቅያን የእምነት መግለጫን በተመለከተ ካለው ከዚህ አሠራር ጋር በመስማማት፣ ግሎባል ሜቶዲስቶች “እና ከወልድ” የሚለውን ሐረግ “መንፈስ ቅዱስ” ከተሰኘው አንቀጽ III የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር ሊያስቀሩ ይችላሉ። የእምነት አንቀጾቹ በመጽሐፍ ቅዱስ የተረጋገጡ ናቸው፤ በቤተ ክርስቲያናችንም ውስጥ ልናስተምራቸው ይገባል። እነዚህ “ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ለዘላለም በአደራ የተሰጠውን እምነት” (ይሁዳ 3) የሚያውጁ መሥረታዊ መለኪያ ናቸው፤ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የአገልግሎት ሕይወት በሚመራን ታማኝ መመሪያ ውስጥ እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለማክበር መሠረት በመጣልም ከሐሰት ትምህርት አማኙን ይጠብቃሉ።

## I. ስላሴ

በአንድ ቅዱስና ሕያው እግዚአብሔር እናምናለን፤ እርሱ ዘላለማዊ፣ ስጋዊ አካልና በብልቶች ያልተከፈለ፣ የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ የፈጠረ ነው። እርሱ በኃይል፣ በጥበብ፣ በፍትህ፣ በቸርነትና በፍቅር ወሰን የለሽ ነው፤ ለስሙ ክብር ለሁሉም መዳን በቸርነት ይገዛል። አንዱ እግዚአብሔር ራሱ፣ ራሱን በሶስት አካላት እንደሚገልጽ፤ እነርሱም የተለዩ ቢሆኑም የማይነጣጠሉ፣ በሕልውና፣ በግርማ፣ በኃይልና በክብር ለዘላለም አንድ የሆኑ ናቸው፤ እነርሱም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው።

## II. ኢየሱስ ክርስቶስ

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ፤ ፍጹም ሰው እንደሆነ፣ ሥጋ በሆነው ዘላለማዊ ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፤ በእርሱ መለኮታዊና ሰብዓዊ ተፈጥሮዎች ያለ መከፈል፣ ያለ መቀላቀል ወይም ያለ መለወጥ ፍጹም በሆነና በማይነጣጠል ሁኔታ ተዋሕደዋል። መለኮታዊ ተፈጥሮውን በተመለከተ፣ በማንነት ከአብ ጋር አንድና ተመሳሳይ ነው። ሰብዓዊ ተፈጥሮውን በተመለከተ፣ በሰብዓዊ ማንነቱ ከእኛ ጋር አንድና ተመሳሳይ ነው፤ ነገር ግን ኃጢአት የለበትም። ለዘለአለም ብቸኛው የእግዚአብሔር አብ የበኩር ልጅና በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ከድንግል ማርያም የተወለደ ነው፡፡ በእውነት መከራን ተቀብሏል፣ ተሰቅሏል፣ ስለ ኃጢአታችንም ሞቷል፣ እና በአካል ከሙታን ተነስቷል። ወደ ሰማይ ዙፋን ከአረገ በኋላም፣ እርሱ ዘላለማዊ አዳኛችንና አስታራቂያችን ነው፤ በሁሉም ነገር ላይ የሚገዛና በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ በክብር የሚመለስ ነው።

እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ እንደነበር እናምናለን። አንድ ጊዜ የቀረበው የክርስቶስ መሥዋዕት ለዓለም ሁሉ ለውርስና ለተግባር የሀጢአት ይቅርታ፣ ቤዛነት፣ ማስተስረያና ካሣ ነው፤ ለኃጢአትም ከዚህ ሌላ ሊከፈል የሚችል ካሣ የለም።

## III. መንፈስ ቅዱስ

ከአብና ከወልድ ለዘላለም የሚወጣ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። እርሱ በማንነት ከአብና ከወልድ ጋር አንድና ተመሳሳይ ሲሆን፣ በግርማ፣ በኃይልና በክብር ከእነርሱ ጋር እኩል ነው። እርሱ እውነተኛና ዘላለማዊ አምላክ ስለሆነ፣ የእኛ አምልኮና ምስጋና ይገባዋል። መንፈስ ዓለምን ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል። እርሱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመሰክራል፣ በእርሱ እንድናምን ይመራናል፣ ወደ ቅዱሳን ህብረት ቤተ ክርስቲያን ያካትተናል፣ በውስጣችንም በመኖሩ ይቀድሰናል። መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በመሆን ስጦታዎችን ያከፋፍላል፤ ቤተ ክርስቲያንንም በዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ተልዕኮ ለመፈጸም በሚያስፈልጋት ነገር ሁሉ ያበቃታል። መንፈስ ቅዱስ ለሚመጣው ክብር ዋስትና መያዣ ሆኖ፣ አማኞችን ጽናናል፣ ይደግፋ፤ ወደ እውነት ሁሉ ይመራል፤ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንንም ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።

## IV. ፍጥረትና መለኮታዊ አቅርቦት

እግዚአብሔር—አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ሁሉንም ነገር ከምንም እንደፈጠረ፣ ከተፈጠሩትም ነገሮች መካከል በእግዚአብሔር ፈቃድ ያልተፈጠረ አንዳችም እንደሌለ እናምናለን። እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነና ሁሉንም ነገር የፈጠረው ለሰዎች ያለውን ፍጹም ፍቅር በነጻነት በመግለጽ ነው። እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ በኃይሉና በጥበቡ ያለማቋረጥ ያጸናል፣ ያስተዳድራል፣ ይደግፋል። የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድና ኃላፊነት በዚህ የመለኮታዊ እቅርቦት ማዕቀፍ ውስጥ ይሠራሉ።

## V. የሰው ልጅ ተፈጥሮ

የሰው ልጆች በእግዚአብሔር መልክና አምሳል እንደተፈጠሩ፣ የሰዎችም ተፈጥሮ መልካም ሆኖ እንደተፈጠረና ክብር እንደተሰጠው እናምናለን። እግዚአብሔርን ፍጹም በሆነው ቸርነቱ እንድንወደውና እንድናከብረው፣ ሌሎችን እንድንወድ፣ ለእነርሱም መልካም ነገር እንድንመኝና እንድንሠራ ተፈጥረናል። እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረን፤

ለቤተሰብ፣ ለማኅበረሰብና ለፍጥረቱ ባለ አዳራ እንድንሆን ፈጥሮናል፡፡ አሁን በኃጢአት የተበላሸ ሁኔታ ውስጥ ወድቀናል፤ ከመጀመሪያው የጽድቅ ሁኔታም እጅግ ርቀናል። ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ዋጋ ያለው ሆነን እንቀጥላለን።

## VI. ኃጢአት እና ነፃ ጸጋ

የሰው ልጅ ከመጀመሪያው ጽድቅ እንደወደቀና ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደተለየ፣ ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ክፋት እንደሚያዘነብሉ እናምናለን። የመጀመሪያው ኃጢአት፣ የእያንዳንዱ ሰው ተፈጥሮ ብልሹነት፣ ሁላችንም የተወለድንበት ሁኔታ ነው። ኃጢአት የሰብእናችንን እያንዳንዱን ክፍል ያበላሻል። ከቀዳሚ ጸጋ ውጭ ወደ እግዚአብሔር መመለስና እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ ሥራዎችን መሥራት አንችልም። ማንኛውም ያለን በጎ ፈቃድ የሚመጣው በክርስቶስ ባለው የእግዚአብሔር ጸጋ እና በእኛ ውስጥ በሚሠራው መንፈስ ነው።

## VII. ቤተክርስቲያን

የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ጌትነት ሥር ያሉ ምእመናን የሚኖራቸው ኅብረት እንደሆነች እናምናለን። ቤተክርስቲያን በባህሪዋም ሆነ በጥሪዋ አንዲት፣ ቅድስት፣ አለም አቀፋዊት እና ሐዋርያዊት ናት። በእርሷ የእግዚአብሔር ቃል የሚሰበከበትና ቅዱሳት ሥርዓቶች በክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት በአግባቡ የሚፈጸሙበት የቤዛነት ኅብረት ናት። ኤጲስ ቆጶሳት እጅ በመጫን ብቁ ወንዶችንና ሴቶችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለአገልግሎት የሚሾሙበት ስፍራ ናት። ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሥር ለአግዚአብሔር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አምልኮና ክብር ለመስጠት፣ አማኞችን ለማነጽ እና ለዓለም ቤዛነት ትኖራለች።

## VIII. መጽሐፍ ቅዱስ

ሁሉም የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለባቸውና መለኮታዊ ስልጣን ያላቸው መጽሀፍ መሆናቸውን እናምናለን። ብሉይ ኪዳን ከአዲሱ ኪዳን ጋር የሚቃረን አይደለም፤ ምክንያቱም ክርስቶስ በሁለቱም ኪዳናት የዘላለም ሕይወት ስለሚሰጠን። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያረጋግጠው ሁሉ እውነተኛ ነው፣ ሙሉ በሙሉ የታመነ ነው፣ ለእምነትና ለተግባርም የማይሳሳት ብቸኛ መመሪያ ነው። ለመዳን የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ ይዟል። በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተገለጠ ወይም በእርሱ ያልተመሠረተ ማንኛውም ነገር ለድኅነት አስፈላጊ ነው ተብሎ ሊወሰድ አይገባም።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ ያደረገው ያው መንፈስ ቅዱስ ራሱ በቅዱሳት መጽሀፍት መስራቱን ይቀጥላላ፤ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማነጽ የቤተ ክርስቲያንን የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም አብርሆትን ይሰጣል። ቅዱሳት መጽሀፍት ለቤተክርስቲያን ወንጌል ስብከት መሰረታዊያንና ለሚሰሙት ሁሉ ዋና የጸጋ መንገድ ናቸው። በቃሉ ስብከት አማካኝነት መንፈስ ቅዱስ ኃጢአታችንን እንድንገነዘብ ያደርጋል፣ ወደ ንስሐ ይጠራናል፣ በክርስቶስ ወዳለ እምነት ይስበናል፣ በእግዚአብሔር መልክም ያድሰናል።

የብሉይ ኪዳን ቀኖናዊ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው፡ ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኍልቍ፣ ዘዳግም፣ ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሩት፣ 1 ሳሙኤል፣ 2 ሳሙኤል፣ 1 ነገሥት፣ 2 ነገሥት፣ 1 ዜና መዋዕል፣ 2 ዜና መዋዕል፣ ዕዝራ፣ ነህምያ፣ አስቴር፣ ኢዮብ፣ መዝሙር፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መሀልየ ዘሰሎሞን፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ ሆሴዕ፣ ኢዮኤል፣ አሞጽ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ሚክያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ ሚልክያስ። የአዲስ ኪዳን ቀኖናዊ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው፡ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ፣ የሐዋርያት ሥራ፣ ሮማውያን፣ 1ኛ ቆሮንቶስ፣ 2ኛ ቆሮንቶስ፣ ገላትያ፣ ኤፌሶን፣ ፊልጵስዩስ፣ ቆላስይስ፣ 1ኛ ተሰሎንቄ፣ 2ኛ ተሰሎንቄ፣ 1ኛ ጢሞቴዎስ፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶ፣ ፊልሞና፣ ዕብራውያን፣ ያዕቆብ፣ 1ኛ ጴጥሮስ፣ 2ኛ ጴጥሮስ፣ 1ኛ ዮሐንስ፣ 2ኛ ዮሐንስ፣ 3ኛ ዮሐንስ፣ ይሁዳ እና ራዕይ።

## IX. ቅዱሳት ሥርዓቶች

በክርስቶስ የተደነገጉት ቅዱሳት ሥርዓቶች የውስጣዊና መንፈሳዊ ጸጋ ውጫዊና የሚታዩ ምልክቶች እንደሆኑና የክርስቲያኑ የእምነት መግለጫ ቃል ኪዳኖች ወይም ምልክቶች ብቻ እንዳልሆኑም እናምናለን። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር የሚያሳዩ ናቸው። እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ያለንን እምነት ሕያው ለማድረግ፣ ለማጠናከር እና ለማረጋገጥ በእኛ ውስጥ የሚሠራበት ልዩ የጸጋ መንገድ ናቸው።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተደነገጉ ሁለት ቅዱሳት ሥርዓቶች ብቻ እንዳሉ እናምናለን፤ እነርሱም ጥምቀትና የጌታ እራት ናቸው።

### *ስለ ጥምቀት*

ወደምትታየው ቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ ወደሆነው አዲስ ኪዳን መግባትን የሚያመለክት አንድ ጥምቀት እንዳለ እናምናለን። ጥምቀት ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር ባለን ኅብረት ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ መካተታችን የሚያሳይ ምልክትና ማኅተም ነው። ጥምቀት ማለት ንስሐ መግባትን፣ ከኃጢአት መንጻትን እና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አዲስ ልደት ማግኘታችንን ያመለክታል። የአዲሱ ኪዳን ተስፋዎች የአማኞችን ልጆች እንደሚያካትቱ፣ ስለዚህም ሕፃናት ለክርስቲያናዊ ጥምቀት ተገቢና ተቀባይነት ያላቸው እንደሆኑ እናምናለን፤ ሕፃናትም ጥምቀት ሊከለከሉ አይገባም። የእምነታቸውን ይፋዊ መግለጫና ለዕድሜ ልክ ደቀ መዝሙርነት ያላቸውን የግል ቁርጠኝነት የሚያሳይ የጥምቀታቸው ማረጋገጫ ላይ እንዲያደርጉ የተጠመቁ ልጆችን ማሳደግና መምራት የቤተ ክርስቲያን ልዩ ኃላፊነት ነው።

### *የጌታ እራት*

የጌታ እራት በእግዚአብሔር የድኅነት ሥራዎች ውስጥ ተካፋይዎች የምንሆንበት የቤዛነታችን ቅዱስ ሥርዓት እንደሆነ እናምናለን። ቅዱስ ቁርባን የክርስቶስን ስቃይና ሞት መታሰቢያ እንዲሁም ክርስቲያኖች ከክርስቶስና እርስ በርሳቸው ያላቸውን ፍቅርና አንድነት የሚያሳይ ምልክት ነው። ምንም እንኳ ቅዱስ ቁርባን ለማዘጋጀት የምንጠቀምባቸው ቁሳዊ ግብአቶች በራሳቸው ሊመለኩ የማይገባቸው ቢሆንም፣ መንፈስ ቅዱስ በቅዱስ አሰራሩ አማካኝነት የክርስቶስን ስጋና ደም እንደ አንድ ጸጋን የምንካፈልብት መንገድ አድርጎ ያካፍለናል፤ የእያንዳንዱ ቁሳዊ ግብአቶች ምንነት ግን ሳይለወጥ ይቀራል። ይህን ቅዱስ ሥርዓት በአክብሮት የሚቀበሉ ሰዎች ክርስቶስ እንደገና እስኪመጣ ድረስ በእምነት ከሥጋውና ከደሙ ይካፈላሉ።

## X. የሕዝብ አምልኮ እና የጌታ ቀን

መለኮታዊ አምልኮ ለቤተ ክርስቲያን ቀጣይነት አስፈላጊ እንደሆነና የሁሉም ክርስቲያኖች ግዴታና መብት እንደሆነ እናምናለን። የጌታ ቀን ለሕዝባዊ አምልኮና የክርስቶስን ትንሣኤ ለማስታወስ በእግዚአብሔር የተደነገገ ነው። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር አዘውትሮ መሰብሰብ ለመንፈሳዊ እድገታችንና ለመቀደሳችን አስፈላጊ ነው። የሕዝብ አምልኮ ሥርዓት እንደየ አከባቢው ማኅበረሰብ ፍላጎት መሠረት በቤተ ክርስቲያን ሊሻሻል እንደሚችል እናምናለን። አምልኮ ሁልጊዜ ሰዎች በሚገባቸው ቋንቋና ቅርጽ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በሚስማማ መልኩ እና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ መሠረት መካሄድ አለበት።

## XI. ንስሐ

መንፈስ ቅዱስ ዓለምን ስለ ኃጢአት እንደሚወቅስና ከከፋት በክርስቶስ ወዳለ እምነት እንድንመለስ እንደሚያስችለን እናምናለን። እውነተኛ ንስሐ ከፋትን በመተውና ኃጢአትን በመናዘዝ፣ እንዲሁም በጸጋ ወደምንካፈልብትና መልካምን ስራ ለመስራት ወደምንከታተልበት ሁኔታ የምንመለስበት ነው፡፡ ይህ በእግዚአብሔር የሚሰጥ የትሕትና መልክ ሲሆን ይህም ለማያምኑት ሰዎች ለጽድቅ ዝግጅት ሆኖ ሲሰጥ፣ ለሚያምኑት ደግሞ በቅድስና የምናደርገውና ከክርስቶስ ጋር ወደ ጥልቅ ህብረት የምንገባበት ዘላቂ ጸጋ ነው።

## XII. መጽደቅ እና ዳግም መወለድ

መጽደቅ ማለት ኃጢአቶቻችንን ይቅር እንደተባሉልንና በክርስቶስ ስራ በፊቱ ጻድቃን ተብለን እንደምንቆጠር እግዚአብሔር በቸርነቱ የሚያውጀው አዋጅ መሆኑን እናምናለን። ይህ የጽድቅ አዋጅ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻና በጸጋ ብቻ ወደኛ ይደርሳል፡፡ መጽደቅ የራሳችን መልካም ሥራዎች ወይም የግል ብቃታችን ውጤት አይደለም፤ ምክንያቱም በመስቀል ላይ ከቀረበው የክርስቶስ የሥርየት መሥዋዕት በስተቀር የመለኮታዊ ፍትሕን መስፈርቶች ሊያሟላ የሚችል ምንም ነገር የለም፤ ከእርሱም በቀር ከውርስ ወይም በግል ከተፈጸመ ኃጢአት ሊያነጻን የሚችል ምንም ነገር የለም። ስለዚህ ክርስቶስን በእምነት እንድንቀበልና እርሱን የግል ጌታችንና አዳኛችን አድርገን በሙሉ ልብ እርግጠኛ ሆነን እንድናምን ተጋብዘናል፡፡ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጆችና የዘላለም ሕይወት ወራሾች ሆነናል። በእምነት ብቻ መጽደቃችን እጅግ ጠቃሚ ትምህርትና የምንጽናናበት ጉዳይ ነው።

ዳግም ልደት በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በጽድቅ የሚደረግ ውስጣዊ መታደስ እንደሆነ እናምናለን። ዳግመኛ ካልተወለድን በስተቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ማየት አንችልም። በአዲስ ልደት ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀናል፣ የመለኮታዊ ባህሪ ተካፋዮች እንድንሆን ተደርገናል፣ በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እንድንለማመድና እርሱን በፈቃዳችንና በፍቅር እንድናገለግለው አስችሎናል። ዳግም መወለድ የመጀመሪያ መቀደሳችን ነው፤ ከዚያም በኋላ በፍቅር ፍጹም ለመሆን ቀስ በቀስ ስንጥር በቅድስና እንታደሳለን።

## XIII. መልካም ሥራዎች

መልካም ሥራዎች ከዳግም ልደት በኋላ የሚመጡና አስፈላጊ የማመናችን ውጤቶች እንደሆኑ እናምናለን፤ ነገር ግን ኃጢአቶቻችንን የማስወገድ ወይም መለኮታዊ ፍርድን የማስቀረት ብቃት የላቸውም። በክርስቶስ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስደስቱና ተቀባይነት ያላቸው መልካም ሥራዎች ከእውነተኛና ሕያው እምነት እንደሚመነጩ እናምናለን። እምነታችን በመልካም ሥራዎቻችን ይገለጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ ከታዘዙት ውጭ ከአማኞች የሚጠበቅ ምንም አይነት መልካም ሥራ የለም። መልካም ሥራዎቻችን እግዚአብሔር ውለታ እንዲያደርግልን አያስገድዱትም፣ እንዲሁም ለሌሎችም ደግነትን ለማድረግ አያስገድዱትም።

## XIV. ሁለንተናዊ ቅድስና

ሁለንተናዊ መቀደስ የፍጹም ፍቅር፣ የጽድቅና የእውነተኛ ቅድስና ደረጃ እንደሆነ እናምናለን። ይህ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚፈጸም የእግዚአብሔር ጸጋ ሥራ ነው። ሁለንተናዊ ቅድስና በክርስቶስ በማመን የምንቀበለውና ሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች በትጋት ሊፈልጉው የሚገባ ነገር ነው። ከእግዚአብሔር የተወለዱ ሰዎች ከኃጢአት ኃይልና ተጽዕኖ አስቀድሞ ነፃ ወጥተዋል። ከዚያ በኋላ ከውርስ ኃጢአት ይነጻሉ፤ እንዲሁም የውርስ ሀጢአት በሐሳብ፣ በቃልና በሥራ ከሚያመጣው ውጤት ይነጻሉ። እንደነዚህ ያሉት አማኞች አሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው፣ ነፍሳቸው፣ ሀሳባቸውና በፍጹም ኃይላቸው መውደድና ባልንጀሮቻቸውን እንደራሳቸው መውደድ፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር ቅዱስ ትእዛዛት ያለ ነቀፋ መመላለስ ይችላሉ።

የመቀደስ ሂደት፣ በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አማካኝነት ሙሉ በሙሉ የሚቀድሰውን ጸጋ ለመቀበል መንገድ ያዘጋጃል። ፍጹም ፍቅር ወይም ክርስቲያናዊ ፍጹምነት የጋራ ከሆኑ ድክመቶች፣ ካለማወቅ ወይም ከስህተቶች፣ እንዲሁም ወደፊት ኃጢአት ልንፈጽም ከምንችልበት ሁኔታ ሁሉ ነፃ እንደማያደርገን እናምናለን። ልባቸው ንጹሕ የሆኑ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል በቅድስና በመኖር፣ በተለይም በመንፈሳዊ ትዕቢት መልክ ከሚመጡ ቀጣይ ፈተናዎች ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው።

## XV. ፍርድ እና የወደፊቱ ሁኔታ

ክርስቶስ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ዳግመኛ በክብር እንደሚመጣ እናምናለን። በሥጋ ትንሣኤ እናምናለን፤ ክፉዎች ለዘላለማዊ ኩነኔ፣ ጻድቃንም በእግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት ውስጥ ለዘላለም ሕይወት ይነሣሉ።

---

2026 ሴፕቴምበር 5 ቅዳሜ ዕለት በደቡብ አፍሪካ፣ ጆሃንስበርግ በተካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ጸድቋል።